# የኢሳፕ ዜና መጽሔት ESAP FLASH

ቅፅ 2 / Issue 2 ታህሣሥ 2006 / January, 2014

ውድ አንባቢ፤



በመስከረም ወር የመጀመሪያ ዜና መጽሔታችንን በተሳካ መልኩ ወደ እናንተ ስናደርስ በየሦስት ወራቱ በወቅታዊ መረጃዎች ደጋግመን እንደምንገናኝ የገባነውን ቃል ጠብቀን እነሆ ሁለተኛውን እትም ይዘንላችሁ መተናል። ባሳለፍነው ሩብ ዓመት ብዙ ነገሮች ተከናውነዋል። የስራ አመራር ኤጀንሲ የሚያገኘው በጀት በመጨመሩ ምክንያት አርባ ዘጠኝ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮቻችን በሚያካሂዷቸው ፕሮጀክቶች አማካኝነት በኢትዮጵያ ውስጥ ሽፋናችን ወደ 224 ወረዳዎች አድጓል። ከአዳዲሶቹ 19 የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋሮቻችን ለተውጣጡ ሰልጣኞች በጀት ከመለቀቁ በፊት የምንሰጠውን ልዩ ስልጠና በጥቅምት ወር በአዳማ ከተማ አካሂደናል። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን የማህበራዊ ተጠያቂነት ወቅታዊ እንቅስቃሴ በተጨባጭ ለመረዳት እንዲቻል የሥራ አመራር ኤጀንሲ ሰራተኞቻችን ከሚመለከታቸው የመንግስት አካላትና ለጋሽ ድርጅት ተወካዮች ጋር በመሆን ስልታዊ የመስክ ጉብኝት እንደ አስፈላጊነቱ አካሂደዋል። የስራ አመራር ኤጀንሲ እንቅስቃሴዎቹን አስመልክቶ አጫጭር ገለጻዎችን አድርጓል። በየገለጻዎቹ በኢትዮጵያ ውስት የማህበራዊ ተጠያቂነትን ሥራ በግንባር ቀደምትነት የሚያከናውኑትን አንድ ወይም ሁለት አጋር ድርጅቶችን በዋነኛነት አሳትፏል። ለሁለተኛ ጊዜ የደረሰቻችሁ ይህቹ ዜና መጽሔት የምትጠብቁትን መረጃ እንደምታደርሳችሁ ተስፋ እያደረግሁ እግረ መንገዴን የሥራ አመራር ኤጀንሲው እንቅስቃሴ ላይ በትጋት የምትሳተፉ አንባቢዎች ሁሉ በመስክ ላይ ከምታገኟቸው ልምዶች መካከል ቀልብ የሚስቡትን እየመረጣችሁ ከፎቶግራፍ ጋር ብትልኩልን ወደፊት በዜና መጽሔታችን በማሳተም በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈፃሚ አጋር ድርጅቶች ልምዶቻችሁን እንዲጋሩ እናደርጋልን።

መልካም የገና በዓል እና አዲስ ዓመት
ሮልፍ ሁኒንክ ፣ የኢሳፕ 2 ቡድን መሪ

*Dear Reader,*

*Following the successful launch of our first Newsflash in October, we promised to come back to you with up-to-date news on Social Accountability (SA) developments every three months. With this second Newsflash we redeem our promise.*

*Many things have happened in the previous quarter. The overall budget for SA activities has since increased considerably resulting in a current coverage of 224 woreda's in Ethiopia where 49 SA Implementing Partners are active. A special pre-disbursement training for representatives of our 19 new SAIPs was organized in Adama in October. Systematic field trips by MA staff members, occasionally accompanied by government and/or donor representatives, took place to learn from the field about the current status of SA in Ethiopia. The MA also organized at frequent intervals ad-hoc presentations on SA but always involving one or more of our SAIPs as they are the implementors of SA in Ethiopia.*

*I do hope that this second Newsflash meets your expectations and I take this opportunity to call on all of our readers in the field who are actively involved in SA implementation to send to us interesting field experiences together with pictures which we then can publish in future Newsflashes, and share with other SAIPs operating elsewhere in Ethiopia.*

*Wishing all of you a Merry Christmas and a Happy New Year*
*Rolf Hunink, ESAP2 Team Leader*

## ተሞክሮ ከመስክ

## Stories from the Field



ድሮ /Before



አሁን/After

Courtesy of MWA

## ትምህርትቤቱን ዝናብ አፍርሶት አልቀረም

የአይሲድ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትቤት ከስድስት ጎጥ ለሚመጡ 360 ልጆች ብቸኛ ትምህርት ቤት ነው። ይህ በቤኒሻንጉል ክልል በጉባ ወረዳ በአይሲድ ቀበሌ የሚገኘው ትምህርት ቤት በሳርና በእንጨት በባህላዊ መንገድ የተሰራ ሲሆን፤ ትምህርት ቤት ለመምጣት ተማሪዎች ለሰአታት በእግር መጓዝ አለባቸው። ባለፈው ክረምት ይህ ብቸኛ ትምህርት ቤት ከባድ ችግር ገጠመው። የክረምቱ ዝናብ የተወሰተን ክፍሎች አፈራረሰው። በጋ ደርሶ ትምህርት ሊጀመር ሆነ።

ወደ ገጽ 5 ዞሯል ...

## The School that Survived the Storm

Isid Primary School is the only primary school for 360 students from six villages in Isid kebele Guba wereda Benishangul region. Students have to walk for hours to come to the school. The school is traditionally built with long grass and wood. Last winter, the school faced a big challenge. Heavy rains demolished some of the classrooms, and it was time to start class.

*continued on page 5 ...*

# ዜና News

## ስኬታማ ፱ኛው የጋራ ግምገማና የትግበራ ድጋፍ፣ የጋራ የበጀትና እርዳታ ግምገማ ስብሰባ

በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ መርሃ ግብር የልማት አጋሮች ስም፣ ፱ኛው የጋራ ግምገማ እና የትግበራ ድጋፍ፣ እንዲሁም የጋራ የበጀትና የእርዳታ ግምገማ ስብሰባ ከሕዳር 2 እስከ ሕዳር 6፣ 2006 ዓ.ም. በፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በአዲስ አበባ ተካሂዷል። በዓመት ሁለት ጊዜ የሚካሄደው ይህ የጋራ ግምገማ ስብሰባ በመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ መርኃግብር እውን ስለተደረጉ አበይት ክንዋኔዎች ሪፖርት የማቅረቢያ ወሳኝ ወቅት ነው።

ማኅበራዊ ተጠያቂነት የመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ዐብይ አካል እንደመሆኑ፣ የሥራ አመራር ኤጀንሲው እና የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር፣ እንዲሁም ከፈፃሚ አጋሮቻችን አንዱ የሆነው የአዲስ አበባ ሴቶች ማኅበር በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተጠያቂነት ያለበት ሁኔታ ላይ ያተኮሩ ገለፃዎችን አቅርበዋል። ከእነዚህ በተጨማሪ፣ ማኅበራዊ ተጠያቂነትን ወደፊት ተቋማዊና ዘላቂ ማድረግ በሚቻልበት ሁኔታ ላይ ትኩረት አድርገው በቀረቡ ገለፃዎች በማኅበራዊ ተጠያቂነት፣ በፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት እና በቅሬታ አፈታት ስልት መካከል ያሉ ጉድኙቶች ተዳስሰዋል።

እንደሚታወቀው፣ ማኅበራዊ ተጠያቂነት በመሰረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ ‹‹ዛፍ›› ላይ በቅርቡ ያቆጠቆጠ ‹‹ቅርንጫፍ›› ነው። ማኅበራዊ ተጠያቂነትን ልዩ የሚያደርገው በመሠረታዊ አገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች መካከል እንደ ድልድይ ሆነው የሚሠሩ የህዝባዊ አገልግሎት ድርጅቶች ዐብይ ሚና በሚጫወቱበት ከታች ወደላይ የተዘረጋ ሥርዓት የሚተገበር መሆኑ ነው። በመጪዎቹ ጊዜያት የአገልግሎት ሰጪዎችና ተጠቃሚዎች ግንኙነት እንዲጠናከርና ኢትዮጵያ ውስጥ ለህዝብ የሚቀርቡ መሠረታዊ አገልግሎቶች አቅርቦትና ጥራት እንዲሻሻል የማድረግ ፍላጎት አለ።

> “ማህበራዊ ተጠያቂነት የተለየ ፕሮጀክት አይደለም፤ የመልካም አስተዳደር ፕሮግራማችን ማእከላዊ ምሰሶ ነው።”

ወደ ገጽ 8 ዞሯል . . .

## Successful 9th Joint Review and Implementation Support (JRIS) and Joint Budget and Aid Review (JBAR) Session

On behalf of the Ministry of Finance and Economic Development (MoFED) and the Promotion of Basic Services (PBS) Development Partners, the 9th JRIS/JBAR was organized between 11-15 November at MoFED in Addis Ababa. The semi-annual review session is a key moment to report on the milestones achieved under the PBS program.



Courtesy of MoFED

Social Accountability (SA) is an important element of PBS. A presentation by the Management Agency (MA), together with MoFED and one of our SAIPS, the Addis Ababa Women Association, exposed the progress on SA in Ethiopia. The mutual linkages between SA, Financial Transparency and Accountablity (FTA) and the Grievance Regress Mechanism (GRM) were also discussed in a separate presentation focusing on the future institutionalization and sustainability of SA.

SA is the latest “shoot” at the PBS “tree” which started only recently. Its uniqueness is the fact that it works bottom up with a prominent role for civil society organizations who act as interface between providers and users of basic services. In the period to come, it is intended to strengthen relations between both service providers and users of the services resulting in a qualitative improvement of basic services to be delivered in Ethiopia.

> “Social Accountability is not a separate project; it makes the center pillar of our good governance program.”

continued on page 8...

## የስራ አመራር ኤጀንሲ ከ 19 ተጨማሪ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች ጋር ስምምነት ተፈራረመ፣ ስልጠና ሰጠ፣ የገንዘብ ድጋፍም አደረገ

የማኔጅመንት ኤጀንሲ የውል ስምምነት ለማድረግ የሚያስችለውን ድርድር ካጠናቀቀ በኋላ ከ19 ተጨማሪ የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች ጋር የፕሮጀክት ውል ስምምነት ተፈራረመ። ስምምነቱ የኢትዮጲያ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮግራምን የሚተገብሩ አጋር ድርጅቶችን ቁጥር ከ30 ወደ 49 አሳድጎታል። ስምምነቱ የማኔጅመንት ኤጀንሲው ለአዲሶቹ 19 የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች የ4.7 ሚ የአሜሪካን ዶላር ገንዘብ ድጋፍ እንዲሰጥ ያስችላል። የማኔጅመንት ኤጀንሲ ለአጠቃላይ 49 አጋር ድርጅቶች የሚሰጠው የገንዘብ ድጋፍ በጀት 13.5 ሚ የአሜሪካን ዶላር ሲሆን፣ የስድስት ወር ፕሮጀክታቸውን እንዲያካሂዱበት የማኔጅመንት ኤጀንሲው እስከዛሬ ድረስ በ3ተኛ እና በ4ኛው ሩብ አመት ለ28 የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች 1.5 ሚ የአሜሪካን ዶላር ሰቷዋል።

የማኔጅመንት ኤጀንሲው ለኢሳፕ 2 ስኬታማነት እንዲረዳ ውሉን ለተፈራረሙ ለአስራ ዘጠኙ አዳዲስ አጋር ድርጅቶች በአዳማ ስልጠና ሰቷዋል። ስልጠናው በጥርና የካቲት 2006 ዓ.ም. ለ30 አጋር ድርጅቶች ከተሰጠው ስልጠና የተገኘውን ተሞክሮና እስካሁን ከተደረጉ ክትትሎችና የአቅም ግንባታ ተግባራት የተገኙትን ልምዶች ያካተተ "ሪያሊቲ ትሬኒንግ" የተባለ በአዲስ መልኩ የተቀረጸ ስልጠና ነበር (ገጽ 6 ላይ ትምህርት በተግባርን ይመልከቱ)። ልዩ ልዩ የማሰልጠኛ መመሪያዎች ተሻሽለው የተሰሩ ሲሆን ለእያንዳንዱ የሥራ መስክ የሚሆኑ የመልመጃ መጽሐፎች ተዘጋጅተዋል። በስልጠናው ላይ የክልል ፋይናንስ ግልጽነትና ተጠያቂነት አስተባባሪዎች፣ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተወካዮችና የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ተሳትፈዋል። ሥልጠናው በተቀመጡለት መስፈርቶች ተገምግሞ እጅግ ተግባራዊና ለኢትዮጲያ ማህበራዊ ተጠያቂነት መርሀ ግብር (ኢሳፕ 2) ሥራ የሚጠቅም መሆኑ ተረጋግጧል።

## The MA Signed Agreement with 19 Additional SAIPs, Provided Training and Disbursed Money

The Management Agency finalized the negotiation process and contracted 19 new Social Accountability Implementing Partners (SAIPs) taking the total tally of SAIPs in ESAP2 from 30 to 49. The agreement will enable the MA to provide an extra grant amount of approximately USD 4.7 Million to the newly contracted SAIPS, the total grant amount for all 49 partners being approximately USD 13.5 Million. So far, in Quarter 3 & 4 the MA disbursed USD 1.5 Million to 28 SAIPs for their project implementation for six months.




Photo by MA Staff

In order to assist our partners in implementing ESAP2 more successfully, the MA provided training for the 19 newly contracted SAIPs in Adama. Taking lessons from the training for the 30 SAIPs in Jan-Feb 2013, as well as from ongoing capacity development and monitoring, a complete redesign of the training process was developed (see "reality training" on page 7). The various MA manuals were updated and training workbooks created for each position in the project team. Regional Financial Transparency and Accountability (FTA) coordinators, MoFED representatives and the Charity and Societies Agency joined this training. The evaluation shows that the new training design was very practical and will help in the implementation of ESAP2.

## የማህበረሰብ ተጠያቂነት እንቅስቃሴ የዲ.ኤፍ.አይ.ዲ አፍሪካ ባልደረቦችን አስገረመ

ከአፍሪካ የተለያዩ አገራትና ከብሪታንያ የተውጣጡ የዲ.ኤፍ.አይ.ዲ. ሰራተኞች የማህበረሰብ ልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የግጭት አፈታት አማካሪዎች በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለውን የማህበራዊ ተጠያቂነት እንቅስቃሴ በተግባር ጎብኝተው ተደነቁ ።

የዲ.ኤፍ.አይ.ዲ. ሰራተኞች በጥቅምት ወር 2006 ዓ.ም. የመጨረሻው ሳምንት ውስጥ ዲ.ኤፍ.አይ.ዲ. በአዲስ አበባ ከተማ ባዘጋጀው ሥልጠና ላይ ሊሳተፉ የመጡ ሲሆን፣ የስራ አመራር ኤጀንሲ ጥቅምት 29 ቀን የማህበራዊ ተጠያቂነት እንቅስቃሴዎችን ለእንግዶቹ አስጎብኝቷል። ጎብኚዎቹ የኢሳፕ2 አጋሮች አዲስ አበባ ሴቶች ማህበር ላይቭ አዲስ እና ውመን ሰፖርት አሶሴሽን በሚሰሩባቸው በጉለሌ እና ቂርቆስ ክፍለ ከተሞች ተዘዋውረው ዜጎችንና አገልግሎት ሰጪዎችን

ወደ ገጽ 4 ዞሯል . . .

## DFID Africa Staff Impressed with Social Accountability in Action

Department for International Development (DFID) staff including social development, governance and conflict advisors came to Addis Ababa from across Africa and the UK to attend a training organised by DFID in the week of 4 November 2013.

The Management Agency arranged a visit on 8 November 2013 for DFID staff to see SA in action. Participants were keen to meet with citizens and service providers and see accountability in action in Gulele and Kirkos sub cities where ESAP2 partners Addis Ababa Women's Association-Live

*continued on page 4...*



Photo by MA Staff

...ከገጽ 3 የዞረ

በማግኘታቸውና ሥራው በተጨባጭ ሲተገበር በመመልከታቸው ተደስተዋል። ጉብኝቱ በኢሳፕ 2 መርሀ ግብር እየተሰራ ያለውን ስራ በተግባር ያሳየ እና ጎብኚዎቹ ከኢትዮጵያ ልምድ እንዲቀስሙ ያስቻለ ነበር። ጎብኚዎቹ ከሰጧቸው አስተያየቶች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

"ቀድሜ ስለፕሮግሙ አንብቤ ነበር። ስፍራው ላይ ተገኝታችሁ እንዴት እየተሰራ እንዳለ እስካላያችሁ፣ ከሰዎቹ ጋር እስካልተነጋገራችሁ፣ የሚሉትን እስካልሰማችሁ ጽንሰ ሀሳቡን ለመረዳት ያስቸግራል። የተሰወረ ነገር ሳይሆን እውነተኛ የህይወት ታሪክ ነው። የሰዎች ህይወት በቀላል የአሰራር ዘዴ ሲቀየር ማየት ያነቃቃል። በአገልግሎት አሰጣጥ ጥቂት ለውጥ ትልቅ ልዩነት ይፈጥራል።"

ሳማንታ ኩፐ
ከዲ.ኤፍ.አይ.ዲ. ዚምባብዌ

"በሩዋንዳም ተመሳሳይ ፕሮግራሞችን እናካሂዳለን። እኛም ዜጎች እና አገልግሎት ሰጪዎች አብረው እንዲሰሩና የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻል እናግዛለን። እዚህ የምትሰሩት ስራ የበለጠ አበረታቶኛል። በእኔም አገር እንደዚህ መስራት ይቻላል።"

ዶሪን ሙዚራንኮኒ
ከዲ.ኤፍ.አይ.ዲ. ሩዋንዳ

"የማህበረሰብ ተሳትፎ አይነተኛ ምሳሌ ነው። ብዙ የማህበረሰብ ተወካዮችን በማሳተፍ ትምህርት ቤቱ ቅድሚያ የሚሰጠውን ነገር የለየበት እንቅስቃሴ ነው። ቀጥሎ የሚሆነውን ማየት ይናፍቃል። ሕብረተሰቡ ውጤትን ለማምጣት እጅግ ተነሳስቷል።"

ማቻ ፋራንት
ከዲ.ኤፍ.አይ.ዲ. ለንደን

"የሴቶች፣ የወጣቶችና ህጻናት ጉዳዮችን ጨምሮ ከፍተኛ የማህበረሰብ ተሳትፎ አለበት... የሚያጓጓ ሂደት ነው"

ዶ/ር ኤምሊን ስኪነር
ከዲ.ኤፍ.አይ.ዲ. ለንደን

...continued from p.3

Addis and Women Support Association are active. The visit helped to showcase the ESAP2 program and visitors learnt from the Ethiopian experience.

*"I have read about the program in advance, it is difficult to understand until you see it yourself, speak to the people and hear about how it works on the ground. It is real life stories rather than abstract. It is inspiring that people's lives have changed through a simple mechanism. Even a subtle change can lead to big change in reality, in service delivery."*

Samantha Coope
DFID Zimbabwe

*"I came from a similar situation, we are running a similar program and are supporting improvements of service delivery, where citizens and service providers are engaged. I am encouraged to see what you are doing; this can also be done in my country."*

Doreen Muzirankoni
DFID Rwanda

*"It was a very interesting example of community engagement in identifying priorities for the school with a large representation of community members. It would be interesting to see what happens next.... The community is enthusiastic to bring about changes..."*

Macha Farrant
DFID London

*"It is an interesting process ...there is a high level of community engagement, including Women, Youth and Children Affairs."*

Dr. Emmeline Skinner
DFID London

## የክትትልና ምዘና ወቅታዊ ዜናዎች

የኢትዮጵያ ማኅበራዊ ተጠያቂነት መርኃግብር (ኢሳፕ 2) የሥራ አመራር ኤጀንሲ በሁሉም ክልል የሚገኙ 38 ወረዳዎችን ጨምሮ ለ24 የማኅበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ፈፃሚ አጋሮች ድጋፍ ተኮር ጉብኝት አደረገ።

መርኃ ግብሩ በሚተገበርባቸው ወረዳዎች ከመርኃግብሩ ትግበራ በፊት እና በኋላ ለውጦችን ለማነፃፀር የሚያስችል የመነሻ መረጃ ለማግኘት በሚረዳ መልኩ የተቀረፀ አጠቃላይ ሐገርአቀፍ የመነሻ ጥናት ክንዋኔን አጠናቀናል። በጥናቱ የተገኙ መረጃዎች የኢሳፕ2 ምክኑያዊ ማዕቀፍ መመዘኛ ወይም መለኪያዎችን ወቅታዊ ለማድረግ ጥቅም ላይ ውለዋል። አሁን ለማነጻጸሪያነት የሚረዱ የግብ አመልካቾች አሉን። መረጃዎቹ ከዚህም በተጨማሪ የኢሳፕ2 ፕሮጀክትን ከመሠረታዊ አገልግሎቶች ማሻሻያ መርኃግብር አጠቃላይ ማዕቀፍ ጋር ለማስተሳሰር ረድቷል።

## M&E UPDATES

The ESAP2 MA conducted supportive supervisions to 24 SAIPs in 38 woredas in all regions.

We completed the implementation of a comprehensive and nationwide baseline survey that has been designed to provide to enable pre- and post-program comparison in intervention woredas. The data was used to update the ESAP2 logical framework matrix, and we now have indicators with targets that provide points for comparison. It also served to align the ESAP2 project with the overall framework of the Promoting Basic Services Program (PBS).



Babile, Somali



Mettu, Oromia



Mekelle, Tigray



Borena, Amhara

Photo by MA Staff

## ትምህርት ቤቱን . . .

...ከገጽ 1 የቀጠለ

ህበረተሰቡ ተሰበሰቡና በቅድሚያ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር ተወያዩ ። ከዛ በኋላ ሁሉም የሚችለውን አደረገ። ሳርና፤ ዕንጨት ተዋጣ፡ ጉልበት ያለው በጉልበቱ አገዘ። ትምህርት ቤቱን ዝናብ አፍርሶት አልቀረም። መልሶ ተገነባ። ትምህርትም ቀጠለ።

"ህብረተሰቡ ከዚህ ቀደም ሁሉንም ችግር መንግሰት እንዲፈታ ይጠብቅ ነበር። አሁን ግን ህብረተሰቡ ያገባኛል በማለት የራሱን ድርሻ መወጣት ጀምሯል። ይህ የማህበራዊ ተጠያቂነት መርሀ ግብር ያመጣው የግንዛቤ ማሰጨበጫ አንቅስቃሴ ውጤት ነው" ይላል ከኢሳፕ2 አጋር ድርጅቶች አንዱ የሆነው እና በትምህርት ዘርፍ ላይ የሚሰራው የምጀጅጉዋ የሴቶች ማህበር የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ኦፊሰር ዩሱፍ መሃመድ ።

## The School that Survived . . .

*...continued from page 1*

Then, the community held discussions on their needs and priority. They mobilized everyone. Some brought timber, others grass and still others helped with free labor. The school survived the storm and class resumed.

"In the past, the community expected the government to address all the problems in the area, but now the community started playing its part having realized their obligation. This is the result of the social accountability sensitization activities undertaken in the area," says Yosouf Mohammed Project Officer with MujejiGua Women's Association one of ESAP2's partners working on education sector.

# ትምህርት በተግባር

በሉሲያ ናስ
የማህበራዊ ተጠያቂነት ኤክስፐርት፣ ኢሳፕ2

“ከዚህ በፊት ካገኘኋቸው ሁሉ የተሻለ ለሥራዬ እጅግ የሚጠቅመኝን ልምድ ባሳለፍኩት አምስት ቀናት ቀስሜአለሁ ።” ይህ የሥራ አመራር ተቋማችን በጥቅምት ወር የመጀመሪያና ሁለተኛ ሳምንት በአዳማ ኤግዘኪቲቭ ሆቴል ለሁለተኛ ዙር አስራ ዘጠኝ አዳዲስ ማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ አጋር ድርጅቶች የገንዘብ ድጋፍ ከማድረጉ በፊት ባካሄደው ስልጠና ላይ የተሳተፉት ሰልጣኞች ከሰጡት አስተያየቶች መካከል ለአብነት የቀረበ ነው። ይህን ስልጠና ልዩና ተመራጭ የሚያደርገው ምንድን ነው?

የሦስተኛው ቀን ስልጠና ማብቂያ ላይ በነበረው የማኔጅመንት ኤጀንሲ አመቻቾች ውይይት ላይ አንድ ባልደረባችን “ስልጠናው ተጫባጭ ነው። ልክ በወረዳ ውስጥ በሚካሄድ የገጽለገጽ ውይይት ውስጥ በአካል ተገኝቼ የተሳተፍኩ ያህል ነው የተሰማኝ” አለ። የማኔጅመንት ኤጀንሲ ባልደረቦች ስልጠናው ይህን ያህል ውጤታማ ይሆናል ብለው አልገመቱም ነበር። “የፕሮጀክቱን ሰራተኞች በሙሉ በአንድነት አድርጎ ማሰልጠን ውጤት ያመጣ ይሆን? የሂሳብ ባለሙያዎችን ከክትትልና ግምገማ ባለሙያዎች ጋር አብሮ ማሰልጠን ይቻል ይሆን? በወረዳ ደረጃ ሥራውን የሚያስተባብሩትንና የፕሮጀክቱን አስተባባሪዎች በተመሳሳይ ወቅት በአንድ ሳምንት ውስጥ ስልጠና እንዲወስዱ ማድረግ ይቻል ይሆን?” እያሉ ስለስኬታማነቱ ያመነቱም ነበር። ሆኖም ነገሮች በታላቅ ስኬት ተከናወኑ። ምክንያቱም ተሳታፊዎች የተሻለ ትምህርት የሚያገኙት በተቻለ መጠን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚያከነውኑበትን አካባቢ በሚመስል የሥልጠና ሁኔታ ውስጥ ሲገቡ ነው። ስልጠናው የማህበራዊ ተጠያቂነት ፕሮጀክት ዑደትን (Social Accountability project cycle) የተከተለ ሲሆን እያንዳንዱ ቡድን ሥልጠናውን የሚከታተለው ተለይቶ በተሰጠው በራሱ ሥራ ላይ ነው።

ለምሳሌ ከወረዳ አስተባባሪዎች በከፊል ከሰዓት በፊት በውጤት ካርድ አማካኝነት ባሰባሰቡት መረጃ ላይ ተመርኩዘው የገጽለገጽ ውይይት እንዲያዘጋጁ ተጠየቁ። የውይይቱ ተሳታፊዎች በተቻለ መጠን ትክክለኛ የማህበረሰብ አባላትን እንዲወክሉ ለዜጎች፣ ለአገልግሎት ጪዎች፣ እና ለወረዳ ሃላፊዎች የስልጠና አመቻቾች የተለያዩ ሚናዎችን አዘጋጁ። የቀሩት የወረዳ አስተባባሪዎች የውይይቱ ሂደት ወዴት እንደሚያመራ፣ ማን ጠቃሚ ሃሳቦችን እንደሚሰነዝር፣ ማን ተግዳሮቶችን እንደሚያነሳ በማስተዋል ይከታተሉ ነበር። ሂደቱን በማስተዋል መከታተል ብዙ ጊዜ ትኩረት የማይሰጠው ነገር ቢሆንም አመቻቾች ሊኖራቸው የሚገባ አስፈላጊ ክህሎት ነው። በዚህ ጊዜ የፕሮጀክት አስተባባሪዎች ደግሞ ወረዳ አስተባባሪዎቹ የአመቻችነት ሥራቸውን የሚያካሂዱበትን መንገድ እየተከታተሉ ጠቃሚ የሆነ ምላሽ(ግብዓት) ለመስጠት ራሳቸውን ያዘጋጃሉ። የሂሳብ ሰራተኞችም በዚህ የማህበረሰብ ውይይት ውስጥ ተሳታፊ ነበሩ። አንዱ የሂሳብ ባለሙያ “የማህበረሰብ ውይይት ለማዘጋጀት ምን ምን ወጪዎች እንደሚያስፈልጉ ለመረዳት ችያለሁ” ሲል አስተያየት ሰጥቷል። በሥልጠናው ወቅት እያንዳንዱ ሰልጣኝ መማር የሚገባውን ተግባራዊ በሆነ መንገድ ይማራል።

ይህን ዓይነቱን የሥልጠና አቀራረብ “ሪያሊት ትሬይኒንግ” ብለን ልንጠራው እንችላለን። ሁሉም የሥልጠና ክፍለ ጊዜዎች የሥልጠናው ተሳታፊዎች ሄደው ለሚሰሩት ቀጣይ ስራ የበለጠ እንዲታጠቁ ታስበው የተቀረፁ ናቸው። ስልጠናው እንደታሰበው በትክክል መካሄዱ አስደስቶናል። ሆኖም ፍሬው የሚለካው በውጤቱ ነውና አስራ ዘጠኙ አዳዲስ ሳይፓች ከቀደሙት ሰላሳዎቹ ይልቅ በሥራቸው ውጤታማ ይሆኑ ይሆን... (ይቀጥላል)

*ከስልጠናው ብዙ ነገር ተምረናል። መንግስት ቢቀየርም ባይቀየርም መሰረታዊ አገልግሎቶች ከለላ ሊኖራቸው ይገባል። ማህበራዊ ተጠያቂነት ማለት አገልግሎት ሰጪ እና ዜጎች ገንቢ በሆነ መልኩ አብሮ እንዲሰሩ ማድረግ ነው። አገልግሎት ሰጪዎች ለዜጎች ጥያቄ ምላሽ መስጠት አለባቸው። እኛ ሳንሆን ዜጎች እራሳቸው ድምጻቸውን ማሰማት አለባቸው። እኛ ገለልተኛ መሆን አለብን። አለበለዚያ ነገሮች ይበላሻሉ። የማመቻቸት ክህሎት በጣም ጠቃሚ ነገር ነው።ግንዛቤ ለማስጨበጫ እና የገጽለገጽ ውይይት ለማካሄድ ዝግጁ እንድንሆን ረድቶናል።*

*ተስፋዬ አለሙ፣ ፕሮግራም አስተባባሪ፣ ከኢትዮጲያ የህግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር*

*ስልጠናው ፕሮጀክቱን በትክክል እንድተገብር ይረዳኛል። እንደማገኝዋል ያሉ የምንጠቀማቸው መጽሐፎች ተሰቶናል። እታች ያለውን ማህበረሰብ ባገናዘበ መልኩ ነው የተቀረጸው።በደንብ የተቀረጸ ነው። የስልጠናው አሰጣጥ መንገድ ጥሩ ነበር። የሂሳብ ባለሙያዎችን፣ ክትትልና ግምገማ ባለሙያዎችን፣ ሥራውን የሚያስተባብሩትን ሁሉንም ባንድላይ ያሰባሰበ ነበር። የአሰልጣኞቹ አቀራረብ አንደኳደኛ ነው። እኛም ሌላ ስልጠና ስንሰጥ እንጠቀምበታለን።*

*ገዲሳ መሀመድ፣ ወረዳ አስተባባሪ፣ ጅማ ኢፍዳ ኢመርዳ*

*ስለ ማህበራዊ ተጠያቂነት ስሰማ የመጀመሪያ ጊዜዬ ነው። ጽንሰ ሃሳቡንም ራሱ አላቀውም ነበር። መጀመሪያ የመንግስት የስራ ሃላፊዎችን ለመፍረድ እና ለመቆጣጠር መስሎኝ ነበር። በስልጠናው ላይ ከተካፈልነው ልምድ ግን ማህበራዊ ተጠያቂነትን ባሳታፊ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል ። አሁን ወረዳ አስተባባሪዎችን እንኳን አንደማሰለጥን እና እንደምረዳ እተማመናለሁ። ስልጠናው የትኛውን ስልት መምረጥ እንዳለብን ለመወሰን ረድቶናል። ፕሮጀክቱ ምን እንደሚፈልግ ገብቶናል። በተግባር ምን እንደሚያጋጥመን ተረድተናል። በፕሮጀክቱ የሚሳተፉ ሰራተኞች መካከል (ለምሳሌ በሂሳብ ባለሞያዎች እና በፕሮግራም አስተባባሪዎች) መግባባት እንዲኖር አድርጓል።*

*ፈቲሃ አህመድ፣ ፕሮግራም ኦፊሰር፣ ኤስኢዲኤ*





















Photo by MA Staff

## Reality Training

*By Lucia Nass*
*Social Accountability Expert, ESAP2*

*"I have got the best experience in my career in the last 5 days."* This is an example of the great comments the Management Agency received from participants in the pre-disbursement training for 19 new grantees of ESAP2, which was conducted in the first and third week of October 2013, in Executive Hotel, Adama. So, what was so special about this training?

*"It was so real, I almost felt like I was attending the interface meeting in the wereda,"* one of the MA staff said during the facilitators' meeting at the end of the third training day. Initially, the MA facilitators were a bit skeptical: would it work to bring the whole project team together, and to train finance officers together with M&E officers, woreda coordinators and project coordinators in the same week? Well, it worked great, and here's why. Participants learn best when they are put in situations that resemble the real work as close as possible. This training therefore followed the Social Accountability project cycle, and each group of participants was learning about their specific job in the project along the way.

For instance, some woreda coordinators were invited to facilitate an interface meeting, using the findings from the Community Score Card exercise they had conducted in the morning session. During the interface meeting, for which the trainers had prepared various roles for citizens, service providers and woreda officials to make it as real as possible, other woreda coordinators were observing the dynamics in the interface meeting: who was helpful? who was challenging? Observation is an important skill of facilitators that is often overlooked. Meanwhile, the Project Coordinators were observing the facilitation by woreda coordinators and learned to give appreciative feedback. Finance officers attended the interface meeting as well, and one of them commented later: "This gives me a better understanding of the type of costs involved in organizing interface meetings." In this way, everyone was learning what they had to learn in the same practical session.

This approach to learning can be called "Reality Training". All the sessions in the training program are designed so that participants are prepared for their upcoming work. We are pleased that it worked well, but the proof is in the pudding. Will the 19 new SAIPs do better with project start-up than the 30 SAIPs that have started before them? To be continued…

*We have learned a lot from the training. Basic services should be protected whether government changes or not. SA is about constructive engagement of citizens and service providers. Service providers have to be responsive. Citizens themselves have to voice their needs not us. We [SAIPS] have to be neutral, otherwise it may be counterproductive. Facilitation is a very important element; it will help us prepare ourselves in our handling of sensitization and interface meeting.*

Tesfaye Alemu
Program Coordinator
Ethiopian Women Lawyers' Association

*The training will help me implement the project properly. We have reference materials such as the manual. The grassroots level is taken into consideration. It is very structured. The approach is good and it brought everyone on board: woreda coordinators, M& E officers, finance officers etc. The trainers' approach was friendly, we will apply it when we give training elsewhere.*

Gadisa Mohammed
Wereda Coordinator
Jima EIFDDA Emrda

*It is my first time to hear about Social Accountability. I didn't even know about the concept. I thought it was to judge and control local officials but, I learned from the experience shared at the training that it can be done in a participatory way. Now I am confident even to guide and help wereda coordinators. The training helped us decide which tool we should use. We understand what the project demands, what we will face on the ground. It creates understanding among people involved in the project for instance, between program coordinators and finance people.*

Fetiha Ahmed
Program Officer
Sustainable Environment and Development Action

...ከገጽ 2 የዞረ

በስብሰባው ማጠቃለያ ላይ የመዝጊያ ንግግር ያደረጉት የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ዴኤታ እና የማኅበራዊ ተጠያቂነት ጥምር ኮሚቴ ሊቀ መንበር ክቡር ዶ/ር አብረሃም ተከስተ የዜጎች በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ላይ ተሳታፊ መሆን ከመልካም አስተዳደር ምሰሶዎች አንዱ መሆኑን በአጽንኦት ተናግረዋል። “ማህበራዊ ተጠያቂነት የተለየ ፕሮጀክት አይደለም። የመልካም አስተዳደር ፕሮግራማችን ማእከላዊ ምሰሶ ነው። መልካም አስተዳደርን በፌደራልም በክልልም በሁሉም ደረጃ እንድናሻሽል ያግዘናል።” ብለዋል ስለሆነም፣ ማኅበራዊ ተጠያቂነት ለአገሪቱ ልማት በጣም አስፈላጊ እንደመሆኑ አመራር፣ ቁርጠኝነት እና ድጋፍ ሊኖር ይገባል ብለዋል። አክለውም “ የክልል መንግስታት  ለሁለተኛ ዙር ተጨማሪዎቹ 19 የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈጻሚ ድርጅቶች ህዝቡን እንዲያስተባብሩ እና ስራ እንዲጀምሩ ማህበራዊ ተጠያቂነትን እውን እንዲያደርጉ ድጋፍ እንድታደርጉላቸው አበረታታለሁ” ብልዋል።



Courtesy of MoFED

*...continued from p.2*

In the closing remarks, State Minister of MoFED and Chair of the SA Steering Committee, H.E. Dr. Abraham Tekeste, emphasized that the engagement of citizens in service delivery is one of the pillars of good governance. “Social Accountability is not a separate project; it makes the center pillar of our good governance program,” he said. “This initiative helps us improve governance at all levels, federal and local.” He further stated that there should be leadership, commitment and support to the SA component as it is important for the development of the nation. He said: “I encourage the regional governments to support CSOs that are mobilizing citizens; support the second round of 19 SAIPS to be on the ground and to start actualization of SA.”

ይህ በአለም ባንክ የሚተዳደረው በለጋሾች የአደራ ፈንድ ድጋፍ የሚደረግለት የኢሳፕ2 (ESAP2) የዜና መጽሔት ነው።

This is a quarterly newsletter published by the MA of ESAP2 funded by World Bank administered multi-donor trust fund.

MANAGEMENT AGENCY

GOPA | VNG International | YEM – Consultant Institute

Tel. +251-11-6634661, 6634601
Cape Verde st. | P. O. Box 28024/1000
WMA Sets Bldg, 2nd Floor | Addis Ababa, Ethiopia
info@esap2.org.et | Facebook: ESAP2





## ከኢሳፕ2 ዲጂታል አለም

## From ESAP2 Digital World

የኢሳፕ2 የመነሻ ጥናትን ማግኘት እችላለሁ ?

ናትናኤል ፈለቀ

ውድ ናትናኤል፣

ስለ ፕሮግራማችን የማወቅ ፍላጎት ስላለሽ እናመሰግናለን። ጥናቱ በዌብሳይታችን ላይ ስለሚገኝ ከዛ ላይ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል። ታድያ አስተያየትሽን መላክ እንዳትረሺ። www.esap2.org/ esap2facebook

ኢሳፕ2

መልካም አስተዳደርን ማዳበር ስር የሰደደ ድህነትን ለመቀነስና ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ ጥሩ መሳሪያ ነው። ማህበራዊ ተጠያቂነት ይህንን ለማድረግ አንዱ መንገድ ነው። እንደኔ ሀሳብ የኢትዮጲያ ማህበራዊ ተጠያቂነት መርሀ ግብር ይህንን ባህል የማዳበር ግዙፍ ሀላፊነት አለበት። ትልቅም ስራ እየሰራ እነደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ። ነገር ግን በጣም የሚያስፈራኝ በጀት ስትለቁ በጣም ስለሚዘገይ ግቡን እንዳያኮላሸው ነው።

አዲሱ እቲፉ፣ ጉራጌ ልማት መህበር ፕሮጀክት አስተባባሪ

ውድ አዲሱ፣

በመጀመሪያ በጀት በመዘግየቱ ምክኒያት ለተፈጠረው ችግር ከልብ ይቅርታ እንጠይቃለን። በጀት ሲለቀቅ የሚዘገየው በዋናነት የማህበራዊ ተጠያቂነት ፈፃሚ አጋሮቻችን ዘግይተው የፋይናንስ ሪፖርት ስለሚልኩ እና የስራ አመራር ኤጀንሲው የግምገማ ሂደት ረጅም ስለሆነ ነው። የስራ አመራር ኤጀንሲው ተጠያቂ ስለሆነ፣ ሪፖርቶችን በጥልቀት መገምገምን ጨምሮ ጠንካራ የገንዘብ አጠቃቀም ቁጥጥር ስርዓት ማበጀት አለበት። በአሁኑ ሰአት የስራ አመራር ኤጀንሲው የፋይናንሻል ሪፖርት መስፈርቶችን እያቀለለ ይገኛል። አጋሮቻችን ሪፖርታቸውን በጊዜ ካቀረቡና ለሚሰጣቸው አስተያየት ፈጣን ምላሽ ከሰጡ ችግሩ እስከመጨረሻው ሊፈታ ይችላል። ስለምትረዳን እናመሰግናለን። በጋራ ለውጥ እናመጣለን።

ኢሳፕ2

Is it possible to get the finding report of ESAP2 baseline survey?

Natnael Feleke

Dear Natnael,

Thank you very much for showing interest in our program. The ESAP2 Baseline survey is now available online. Just log on to our Website. Please don’t forget to share your feedback. www.esap2.org/ esap2facebook

ESAP 2

Developing Good Governance is one of the best weapons to alleviate deep-rooted poverty and ensure sustainable development in Ethiopia, and the Social Accountability mechanism is an approach to exercise such issues. I think the MA bears huge responsibility to develop such culture, and hope it is doing great. However, I have great fear that budget release is extremely slow which may greatly affect the realization of the objectives.

Addisu Etifu, ESAP-2 Project Coordinator - Guraghe Development Association

Dear Addisu,

First, we sincerely apologize for the inconvenience caused by the delay of fund disbursement. The delay is mainly caused by the delay in submission of financial reports by SAIPs and the lengthy review process by the MA. As the MA is ultimately responsible for the fund utilization, it has to enforce strong financial monitoring system such as reviewing the financial reports in-depth. The MA is now simplifying the reporting requirements. If the SAIPs can also submit reports timely and quickly respond to MA’s comments, it is possible to resolve the problem. Thank you for your understanding and together we can make a difference.

ESAP2

Reha Touch: 091-120 9525